በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር

የ2014 በጀት ዓመት ከጥር1 እስከ ሰኔ 30/2014 ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የፌደራል የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር
ከጥር1 2014 - ሰኔ 30 2014 ድረስ ያለ የሂሳብ
ኦዲት ሪፖርት

የፌዴራል ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የፌዴራል ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የፌዴራል ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በቴያትር ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣
- የተጠቃለለ የሂሳብ ማመዛዘኛ

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የፌዴራል ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የ2014 የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 ቁጥር 4 ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ሊረጋገጥ እንደሚገባ ተገልጿል፡፡ ሆኖም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በድምሩ ብር2,969,486.80 የተሳታፊዎች ዝርዝር ሳይቀርብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2. የፈዴራል መንግሰት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 9 መስረት ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ለክፍያዎች መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች መሟላታቸውን መረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ይገልፃል፡፡ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ብር 25,200.00 የደመወዝ መጠናቸው የሚገልጽ መገጣጠሚያ ደብደቤ ሳይቀርብ ለውሎ አበል የተከፈለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 2 በስተቀር በተገለፁት ሁኔታዎች መሠረታዊነትና ጉልህነት የተነሳ ፌዴራል ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀም በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

ህጋዊነትን ያልተከተሉ ጉዳዮች(Compliance Matters)

3. በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 በግዥ መመሪያ አንቀፅ 15 ንኡስ አንቀጽ 2 በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማንኛውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ

መፈጸም አለባቸው፡፡ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 1 የአዋጁ አንቀጽ 55 እና 56 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥዎች በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው፡፡ ሆኖም ሊታቀዱ ያልቻሉ ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ እና ዋጋቸው ከዚህ በታች በንዑስ አንቀጽ 24.2 በተመለከተው ገደብ ውስጥ ይሆናል ተብሎ የሚገመቱ ግዥዎችን በዋጋ መቅረቢያ የግዥ ዘዴ መፈፀም ይችላሉ፡፡ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 2 በዚህ አንቀጽ ለመጠበቅ ሲባል የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍሎ መግዛት አይኖርባቸውም በሚለው መሰረት በመ/ቤቱ መመሪያው ተግባራዊ ስለመደረጉ ለማረጋገጥ በተወሰደ የኦዲት ናሙና

በድምሩ ብር 2,317,800.00 በሆነ ክፍያ ሰባ ደረጃ ከተባለ ሆቴል በተለያየ ግዜ የሆቴል አገልግሎት የተገኘ ቢሆንም ግዥው በግልጽ ጨረታ መገዛት ሲገባው በመከፋፈል በፕሮፎርማ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

4. የፌደራል መንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001ዓ.ም አንቀፅ 46(2) እንዲሁም ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ 16 ንዑሰ አንቀፅ 24 (ቁጥር2) ላይ የግልፅ ጨረታ አሸናፊውን ድርጅት በማሳወቅ በመንግስት መስሪያ ቤቱና በተጫራቹ መካከል ዝርዝር ጉዳዮችን ያካተተ ውል በመስሪያ ቤቱ ኃላፊ እና በተጫራቹ መፈረም እንዳለበት ይገልፃል፡፡ በዚሁ አዋጅና መመሪያ መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ግዥዎችን እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

ብር 1,025,000.00 ለማክ ኢንተርቴይመንት ግልፅ ጨረታ ሳይወጣ እንዲሁም ውል ሳይገባ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

5. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ይሁን እንጂ በበጀት ዓመቱ ከሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ፤

- ➢ በድምሩ ብር 1,006,039,843.55 በደንቡና በመመሪያው መሰረት ሳይወራረድ የሚገኝ ተሰብሳቢ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

6. በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ፣ በፌዴራል መንግስት መ//ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 የተከፋይ ሂሳብ በአንቀጽ 8 ቁጥር 5 ከፊደል ሀ-ሠ በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እየተከፈሉና እየተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በድምሩ ብር 9,966,508.98. በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)</u>

7. በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀጽ 12(1) ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት መሥሪያ ቤቱ በ2014 በጀት ዓመት የተፈቀደው የወጪ በጀት አጠቃቀም ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ ሥራ ላይ ያልዋለው በየሂሳብ መደቦቹ ሲታይ፡-

ከመደበኛ በጀት ብር ብር 17,918,356.38 ከመደበኛ በጀት ብር 581,266,136.88 ከካፒታል በጀት በድምሩ ብር 599,184,493.26 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ሌሎች ጉዳዮች(Other matter</u>

8. በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች መካከል የሚፈጸም ርክክብ መመሪያ ቁጥር 10/2003 ቁጥር 6 የመንግስት መ/ቤቶች ሲፈርሱ፤ ሲቀላቀሉ/ሲዋሀዱ ፤የሰራ ክፍሎች ከአንድ መ/ቤት ወጥተው ወደሌላ መ/ቤት ሲገቡ፤
   1. ባለቤት የሌላቸው ንብረቶች ሲገኙ፤
   2. የግንባታ ወይም የልማት ፕሮጀክቶች ሥራዎች ከአንዱ የመንግስት መ/ቤት ወደሌላው መንግስት መ/ቤት ሲተላለፉ ርክክብ መደረግ እንዳለበት እንዲሁም በዚሁ መመሪያ ቁጥር 8 ሐ ላይ ርክክብ የሚፈጸምባቸውን ንብረቶች ዝርዝር ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲት መረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል፤

   እንዲሁም የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል አንድ አንቀጽ 5 የመንግስት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግስት ንብረት

በጥንቃቄ የመያዝ፣ የመጠቀም፣ የመቆጣጠር እና አገልግሎት ላይ በማይውልበት ጊዜ በወቅቱና በተገቢው መንገድ ማስወገድ እንዳለባቸው ያዛል። በዚህ መሰረት መከናወኑን ለማየት ኦዲት ሲደረግ፡

- የስፖርት ኮሚሽን ከባህል ሚ/ር ጋር የተቀላቀለ ሲሆን የንብረት ርክክብ የሌለውና የሁለቱም መ/ቤት ንብረቶች በአንድ ላይ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፡ 2014 በጀት ዓመት የንብረት ቆጠራ ያልተከናወነ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

9 የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ክፍል አራት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 የመንግስት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ፣ ቅባት፤ ዘይት አጠቃቀም እና ቁጥጥር በሚለው ስር ‹‹ለበላይ ኃላፊዎች እና ለኃላፊዎች ከሚመደቡ ተሽከርካሪዎች በስተቀር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር መጠን ጋር እየተመዛገበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ መቅረብ እንደሚኖርበት›› መመሪያው ቢያመለክትም፤በሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ስር የሚገኙት ተሽከርካሪዎች በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተጠቀሙት የነዳጅ መጠን የሸፈኑት የኪ/ሜትር ርቀት በየወሩ ምዝገባ እየተከናወነ ተገቢው ሪፖርት እንዲቀርብ ተጠይቆ ያልቀረበ በመሆኑ እንዲሁም ኖርማላይዜሽን ወይም አንድ መኪና በኪሎ ሜትር ምን ያህል ነዳጅ የሚጠቀም እንደሆነ የተጠና መረጃ ባለመቅረቡ መስሪያ ቤቱ ይህንን መሰረት አድርጎ የነዳጅ አጠቃቀም ሪፖርት ያልቀረበ በመሆኑ ምክንያት፤ የአመቱ የነዳጅ ወጪ ሂሳብ ብር 4,823,103.75 አጠቃቀም አግባብነት ማጣራት ያልተቻለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

10. የንብረት አያያዝ አጠቃቀም እና አስተዳደር በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እንዲሁም በፌዴራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መሆኑን የተሽከርካሪዎች የንብረት አያያዝና አጠቃቀም ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ታርጋ ቁጥር 4 -20595 ሚትስቡሽ ፒክአፕ 7 ወር
- ታርጋ ቁጥር 4 -26200 ዲኤፍኤም አውቶሞቢልክ 8 ወር
- ታርጋ ቁጥር 4- 20330 ሚትስቡሽ ፒካፕ 7ወር

- ታርጋ ቁጥር 4- 05668 ቶዮታ ለንድ ክሩዘር ከ1አመት በላይ
- ታርጋ ቁጥር 4 - 08168 ቶዮታ ለንድ ክሩዘር 4ወር
- ቶዮታ ራቭ4 ለረጂም ጊዜ የቆመ መሆኑ
- ታርጋ ቁጥር 4-05988 ሀርድ ቶፕ ለረጂም ጊዜየቆመ
- ታርጋ ቁጥር 4-04301 አውቶሞቢል ለረጂም ጊዜ በብልሽት ምክንያት የቆሙ መሆኑ፤
- ታረጋ ቁጥር 4 -30602 አቫንዛ አቶ ኢሳያስ ጅራ ወደሌላ ቦታ ሲዛወሩ ያልተመለሰ፤
- ታርጋ ቁጥር 4-22808 ቪ8 ላንድ ክሩዘር ሊብሬ የሌለው፤
- ቶዮታ ቪ8 እና ቶዮታ ራቫ 4 ተርጋ ቁጥርና ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፤
- ሂሎ ታክሲየሚሉ 3 አምቡላንሶች ጊቢ ውስጥ የሚገኙና ምንም ዓይነት የርክክብ ማስረጃ እና ሞዴል/19/ ሳይቆረጥላቸው ለረጅም ጊዜ በግቢ ውስጥ ቆመው የተገኙ መሆናቸው
- ላንድሮቨር ኢ.ት 4.01109 ተሽከርካሪ ከ10 ዓመታት በላይ 6 ኪሎበሚገኘው የስብሰባ ማዕከል የቆመ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

11. በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከስቱ ችግሮችንና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የውስጥና የውጪ ኦዲተሮችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ ማካሄድ እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ሆኖም መ/ቤቱ የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ ፣ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የሥጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል::

12. በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 ክፍል ሁለት መሰረት ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ስለመሥሪያ ቤቱ አስፈላጊ መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለመመዝገብ፣ ለማከናወን፣

ለማጠቃለል እና ሪፖርት ለማድረግ እንዲያስችላቸው በኮምፒዩተር በታገዘ የመረጃ ሥርዓት ላይ ተስማሚ ቁጥጥሮችን መዘርጋት እና መጠበቅ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በዚሁ ኢንስቲትዩቱ የሚጠቀምበት የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ (ICT) የመረጃ ሚስጥር ጠባቂነት ታማኝነትና አቅርቦት ሊያረጋግጥ የሚችል የመረጃ ቴክኖሎጂ ቀርጾ ሥራ ላይ ማዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

✓ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መረጃ/ ሠነድ ከሥጋት ነፃ የሚሆንበት የፀደቀ (IT Security policy) የሌለው መሆኑ፤

✓ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ላይሰንስድ የሆነ ፀረ ቫይረስ (Anti-Virus) በኮምፒውተሮች ላይ ያልተጫነ መሆኑ፤

✓ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ውስጥ የተዘጋጀና የጸደቀ “User Account Management Standard” የሌለ መሆኑ፤

✓ መ/ቤቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አደጋ ሲያጋጥም መልሶ የሚቋቋምበት እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ፤

✓ በመ/ቤቱ አደጋ ቢደርስ ተብሎ የተዘጋጀ ወይንም ወይም ፎርማል የሆነና ተዘጋጅቶ የተቀመጠ መመሪያ የሌለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

13. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጥር /2002 ስለ በጀት ዝግጅትና ግምገማ ባወጣው ደረጃ /ስታንዳርድ/ የስልክ ፍጆታ ጣሪያ መሰረት ለመደበኛ ስልክ አጠቃቀም ለየሥራ ኃላፊዎች ወርሃዊ የስልክ ጣሪያ የወጣለት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በመ/ቤቱ የተለያዩ ኃላፊዎች ለሚጠቀሙባቸው መደበኛ ስልኮች በስራ አመራሩ የተወሰነ ወርሃዊ የስልክ ፍጆታ ወይም የገንዘብ መጠን የሚገልጽ በስራ አመራሩ

የተወሰነ ወርሃዊ የስልክ ፍጆታ ጣሪያ ያልወጣለት በመሆኑ ክፍያው በሙሉ ለመ/ቤቱ ጥቅም የዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

14. የፌዴራል ዋና ኦዲተር ከ2008 እስከ 2013 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የተወሰደባቸውና ያልተወሰደባቸው ግኝቶች ሁኔታ ሲጣራ፡-

1. <u>(የቀድሞ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር)</u>

<u>በ2013 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤቶች ላይ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ብር 2,128,449.51</u>

- ብር 117,413.70 በብልጫ የተከፈለ ውሎአበል
- ብር 124,612.29 የሰዐት መቆጣጠሪያ ሳይቀርብ መከፈሉ፤
- ብር 69,621.00 በስራ ገበታ ላይ እያሉ ውሎ አበል መከፈሉ፤
- ብር 6,229.00 የአውሮፕላን ትኬት በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- ብር 1,810,573.52 የያዙ የወጪ ሰነድ ማስረጃዎች ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፤

<u>በ2011 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤቶች ላይ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ብር 181,665.1</u>

- ብር 9,011.60 ወደ ገንዘብ የተቀየረው የዓመት ፍቃድ ላይ ያልተቀነሰ የስራ ግብር ያልተመለሰ መሆኑ፤
- በድምር ብር 16,453.50 ከስራ ውጭ ለሰሩ የሂሳብ ሰራተኞች የምሳና የእራት አበል በሚል አለአግባብ መከፈሉ፤
- በድምር ብር 156,200.00 ያለአግባብ ለላብ መተኪያ በሚል የተፈጸመ ክፍያ

<u>በ2010 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤቶች ላይ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ብር 23,975.4</u>

- ብር 23,000.00 በመመሪያ መሰረት ያልተሰበሰበ ያልተቀነሰ ግብር መሆኑ፤
- ብር 975.40 ብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- በሚኒስቴር ከኃላፊነት የተነሱ ኃላፊዎች ተመላሽ ያልተደረጉ ንብረቶች፡፡ክብር ወ/ሮ ፎዚያ አሚን ሚኒስቴር ዴኤታ፤ አውቶሞቢል ዴፍ የሰሌዳ ቁጥር 04-26139 ብዛት 1በብር 1,111,970.09፣ ክቡር አቶ ራመዳን አሸናፊ ሚኒስቴር ዴኤታ፡- ሳምሰንግ ጋላክሲ ሞባይል ብዛት 1 በብር 21,800.00 በድምሩ ብር 1,133,779.09 ለመ/ቤቱ ተመላሽ ያልተደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>በ2009 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤቶች ላይ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ብር 205,824.14</u>

- ብር 12,240.35 ለለቀቁ ሁለት ሰራተኞች የተከፈለ ደሞዝ ወጪ
- የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ብር 30,187.77
- በድምር ብር 125,434.00 ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በብድር የወሰደ ቢሆንም ክበቡ የወሰደውን ገንዘብ መመለስ ያልቻለ መሆኑ፤
- በድምሩ ብር 37,962.02 ከመመሪያ ውጪ ቅደሜና እሁድ የሰሩበት የትርፍ ሰዓት ክፍያ የፈፀመ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

<u>በ2008 በጀት ዓመት በኦዲት ውጤቶች ላይ እርምጀ ያልተወሰደባቸው ዶላር 492.33 ዩሮ222.68</u>

- 50 ዶላር አውሮፕላን ስላመለጣቸው የትኬት ማስቀየሪያ ከመመሪያ ውጭ በብልጫ የተወራረደ የውጭ ሀገር አበል ተመላሽ አለመደረጉ፤
- ክብርት ወ/ሮ ፊትያ የሱፍ ወደ ጀርመን ሲሄዱ ለመኝታና ለቁርስ ከወሰዱት በብልጫ የተከፈለ ቀሪ € 111.34 ተመላሽ አለመደረጉ፤
- ክብርት ወ/ሮ አይሻ መሃመድ ለስራ ጉደይ ወደ ጀርመን ሲሄዱ ለመኝታና ለቁርስ ከውሰዱት በብልጫ የተከፈለ በድምር €111.34 ተመላሽ አለመደረጉ፤
- የአቶ ጀማል ከድር ወደ ቻይና ስሄዱ ለመኝታና ለቁርስ ከወሰዱት ገንዘብ ላይ በብልጫ የተከፈለ በድምሩ $ 442.328 ተመላሽ አለመደረጉ፡

2. <u>(የቀድሞ ስፖርት ኮሚሽን)</u>

<u>በ2013 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤቶች ላይ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ብር 271,907.3</u>

- ብር 6,382.80 ተመላሽያልተደረገ የኢንሹራንስ ክፍያ፤
- ብር 100,170.00 አለአግባብ የተከፈለ የውሎአበል ክፍያ፤
- ብር 35,851.50 በትርፍ የተከፈለ የምሳ አበል፤

- ብር 22,450.00 በብለጫ የተከፈለ ውሎ አበል ፤
- ብር 35,250.00 በብለጫ የተከፈለ ውሎ አበል ፤
- ብር 1,700.00 በድጋሚ የተከፈለ ውሎ አበል፤
- ብር 24,651.00 አለአግባብ የተከፈለ የውሎአበል ክፍያ፤
- ብር 6,941.00 ማስረጃ ያልቀረበለት ፤
- ብር 38,511.00 በብለጫ የተከፈለ ውሎ አበል ፤

<u>በ2012 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤቶች ላይ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ብር 2797.95</u>

- ኮሚሽኑ የሚመለከተውን የመንግሥት አካል ወይም ኤጀንሲውን ሳያስፈቅድ የግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ሠራተኞች በትርፍ ሰዓታቸው ለሰሩበት በሚል የምሳና የትራንስፖርት አበል ክፍያ ብር 2,797.95 ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- በዋናው ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ ብዛት ያላቸው ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ ቴሌቪዥን፣ ፕሪንተር እና ፋም (የሙቀት) የሚገኙ መሆኑ፤
- አገልግሎት የማይሰጡ ብዛታቸው 140 የመኪና ጎማዎች ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፤
    - 4.በንብረት መጠየቂያ ፎርም (ሞዴል/20) ሳይጠየቁ እንዲሁም በእቃ ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል/22) ሳይሞላ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 299,641.64 አሥራ አምስት ኮምፒዩተሮች ወጪ የተደረጉ መሆኑ፤
- ከኮሚሽኑ ከሥራ የለቀቁ ሠራተኞች በሥራ ላይ በነበሩበት ወቅት ይገለገሉበት የነበረው ዋጋቸው ብር 39,910.56 የሆነ ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች ተመላሽ ሳያደርጉ ከሥራ የለቀቁ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት